# ፔን ኢንተርናሽናል-በቋንቋ *መብቶች ላይ የወጣ የጊሮና ማኒፌስቶ*

*ፔን ኢንተርናሽናል የዐለም ጸሐፍትን ያቀራርባል፡፡ይህ ማኒፌስቶ በፔን ኢንተርናሽናል የትርጉምና የቋንቋ መብቶች ኮሚቴ ጊሮና ውስጥ ፣ግንቦት ፳፻፫ ዓ.ም የተዘጋጀና በ፸፯ ኛው ዐለም ዐቀፍ የልዑካን ጉባኤ፣መስከረም ፳፻፬ዓ.ም የጸደቀ ነው፡፡ማኒፌስቶው ፣ የፔን ኢንተርናሽናልን አስር ዋና ዋና የቋንቋ መብት መሪ መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡*

*፩. ልሳነ ብዙህነት ዋጋ ሊሰጠውና ሊጠበቅ የሚገባው የዐለም ቅርስ ነው፡፡*

፪. *ለሁሉም* ቋንቋዎችና ባህሎች የሚሰጥ ክብር፣ የውይይት ልምድ ለማዳበርና ሰላምን በዐለም ላይ ለማስፈን በሚደረገው ሂደት ውስጥ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

፫. ሁሉም ግለሰቦች ህይወት፣ቋንቋ፣ባህልና ማንነት በሚሰጣቸው የማህበረሰብ ልብ ውስጥ መናገርን ይማራሉ፡፡

፬. የተለያዩ ቋንቋዎችና የተለያዩ ሓሳብን የመግለጫ ዘዴዎች የመግባቢያ መንገዶች ብቻ ሳይሆኑ በውስጣቸው የሰው ልጆች የደጉባቸውና ባህሎች የተገነቡባቸው ምህዳር ናቸው፡፡

፭. ማንኛውም አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ቋንቋውን የአካቢው የስራ ቋንቋ አድርጎ የመጠቀም መብት አለው፡፡

፮. በትምህርት ቤት ውስጥ የሚተገበረው የማስተማሪ ዘዴ የአካባቢው ማህበረሰብ የሚናገረው ቋንቋ ክብር ከፍ እንዲል አስተዋጾ ማድረግ አለበት፡፡

፯. ዜጎች ስለተለያዩ ቋንቋዎች ጠቅላላ እውቀት እንዲኖራቸው የሚገባ ነገር ነው፡፡ምክንያቱም የሌሎችን ስሜት መገንዘብንና ሙሁራዊ ግልጽነትን እንዲሁም ስለ እራስ ቋንቋ ጥልቅ እውቀት እንዲኖር ያደርጋልና፡፡

፰. በሰው ልጆች ዘንድ መከባበርና አንዱ ሌላውን መረዳት እየላቀ እንዲመጣ በሚደረገው ወሳኝ ሂደት ውስጥ ስነጽሑፎችን በተለይም በታላላቅ ባህሎች ላይ የተሰረትን መተርጎም በጣም ጠቃሚ የሆነውን ክፍል ይይዛል፡፡

፱. መገናኛ ብዙሃን፣ ልሳነ ብዙህነትን በአወንታዊ መልኩ ውጤታማ ለማድረግና ክብሩን ለማላቅ፣ ባለ ልዩ መብት ድምጽ ማጉሊያ ነው፡፡

፲. የእራስን ቋንቋ የመጠቀምና መጠበቅ መብት በተባበሩት መንግስታት ዘንድ ከመሰረታዊ የሰው ልጆች መብት እንደ አንዱ ሆኖ መቆጠር አለበት፡፡